# መበረታታት ያለበት ጅምር፤



አቶ ሳሙኤል ጌታቸው ከሚስ. አድሪያና ማግናቶ-ሃሙ (Adriana Magnato-Hamu) ጋር

በቶሮንቶ ከተማ 'የኢትዮጵያ ጓደኞች' (Friends of Ethiopia) ተብሎ የሚታወቅ ቡድን (ግሩፕ) 'ኢትዮጵያን ፍራይደይ' (Ethiopian Friday) የተባለ በአይነቱ አዲስ የሆነ ማህበራዊ እንቅስቃሴና አስተዋጽኦ እያደረገ ነው::

ቡድኑ፥ በወር አንዴ የወሩ 2ኛ አርብ ዕለት ምሽት በቶሮንቶ ከሚገኙ አንደኛው ምግብቤት ወስጥ በተዘዋዋሪ በሚያደርገው ዝግጅት ከኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ውስጥና ከአጠቃላዩ የካናዳ ህብረተሰብ መካከል ጉልህ አስተዋጽኦና ሃላፊነት ያላቸውን ግለሰቦች በየጊዜው በፕሮግራም በተያዘው የምረጡኝ ዘመቻ በደገፍ፥ በበኩሉ የፈቃደኛነት አስተዋፆ ለማድረግ ከቡድናቸው ጋር በኦሃዮና ፊላደልፊያ (Ohio & Philadelphia) ይንቀሳቀስ በነበረበት ወቅት የምረጡኝ ዘመቻው ይጠቀምባቸው ከነበሩት መገናኛዎች አንዱ "ኢትዮጵያን ፍራይደይ" ብሎ የሰየመውን ይመሰል እንደነበር አብራርቶልናል::

የሚስተር ባራክ ኦባማ ፕረዚደንታዊ ምርጫ በድል እንደተጠናቀቀ፥ ሳሙአል ጌታቸው ወደሚኖርበት ቶርንቶ፥ ካናዳ ተመልሶ በጃኗሪ 2009 (January 2009) "ኢትዮጵያን ፍራይደይ"



አቶ ሳሙኤል ጌታቸው ከሚስተር ጃክ ላይተን (Jack Layton) ጋር

የሚለውን ፕሮግራም ጀመረ:: የመጀመሪያው ዝግጅት አይቤክስ ምግብ ቤት ውስጥ የተካሄደ ሲሆን ከዕለቱ ተናጋሪ እንግዶች የኢትዮጵያ ማህበር ፕረዚዳንት ዶ/ር ቡሻ ታኣ፥ የኦንታሪቅ ክ/ሀገር ምክር ቤት አባል የሆኑት ሚስተር. ማይክ ኮሌ (Mike Colle, M.P.P.) የቶሮንቶ ትምህርት ቤቶች ቦርድ አባላት ይገኙበታል::

የሐዋርያ ዘጋቢ ከሳሙአል ጋር ባደረገው የቃል ልውውጥ መረዳት እንደተቻለው፥ በየወሩ



አቶ ሳሙአል ጌታቸው ከ ሚስተር ፍራንክ ዲ ጆንግ (Frank de Jong) ጋር

አጋማሽ አርብ ዕለት ምሽት በየምግብ ቤቶች የሚደረገው ዝግጅት ዋና ዓላማ በየሃላፊነት ፈርጃቸው ንግግር እንዲያደርጉና የኮሚኒቲውን አባላት እንዲያወያዩ ተጋብዘው የሚመጡ እንግዶችን የሃላፊነታቸውና የተጠሪነታቸው ጠንካራ ባለቤቶች እንዲሆኑ ማገዝ ሲሆን በዚያው ልክም ተሳታፊዎች ከእንግዶች ቁም ነገር እንዲቀስሙ ማብቃት ነው ብሏል::

ከዚህ አኳያም ሜይ 8/2009 ዳን ፎርዝ ላይ በሚገኘው ዋንዛ ምግብ ቤት ውስጥ በተካሄደው ምሽት፥ የሐዋርያ ዋና አዘጋጅ ሙሉቀን ሙጨ ከኢትዮጵያ ማህበረሰብ ውስጥ ከተጋበዙት እንግዶች አንዱ ሲሆን፥ የካናዳ አዲሱ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (New Democratic Party of Canada – NDP) መሪ የሆኑት ሚስተር ጃክ ላተን (Jack Layton) እና የኦንታሪዮ ክፍለ ሀገር ግሪን ፓርቲ (Green Party) ተጠሪ ሚስተር ፍራንክ ዲ ጆንግ (Frank De Jong – leader of Green Party of Ontario) ከሥራ ባልደረባቸውና የቶሮንቶ -ዳንፎርዝ ግሪንስ (Toronto-Danforth Greens) አካባቢ እጩ ተወዳዳሪ ከሆኑት ከሚስ አድሪያና ማግናቶ-ሃሙ (Adriana Mugnatto-Hamu ) ጋር በመሆን የዕለቱ የክብር እንግዳ በመሆን የየበኩላቸው የሥራ ድርሻና ሃላፊነት በሆነው ጉዳይ ላይ በምግብ ቤቱ ለተገኙት ተሳታፊዎች ንግግርና ውይይት አድርገዋል::

በመጨረሻም አቶ ሙሉቀን ሙጨ፥ የሐዋርያ ጋዜጣ አዘጋጅና አሳታሚ ሆነው ላበረከቱት አስተዋጽኦ የኦንታሪዮ መንግሥት ምክር ቤት አባል በሆኑት በሚስተር ማይክ ኮሌ (Mike Colle, M.P.P.) ተፈርሞ የተዘጋጀላቸውንና የክፍለ ሀገሩን አስተዳደር አርማ የያዘ የአድናቆት ሽልማት ተቀብለዋል::

ይህ አይነቱ መልካም ጅምርና እንቅስቃሴ ለአካባቢያችን አዲስ ሲሆን እንዲያድግና እንዲስፋፋ መበረታትት ያለበት ነው:: የህብረተሰብ አባላቱ እርስ በርስ ከማቀራረቡ በላይ፥ የአካባቢውን የ ንግድ ድርጅቶች ይጠቅማል፥ አጠቃላይ ማህበረሰቡንም ሃላፊነት ካላቸው የካናዳ ልዩ ልዩ ስብእናዎች የበለጠ በማስተዋወቅ የኮሚኒቲው ጥቅምና ደህንነት እንዲታሰብ ያደርጋል:: በየዝግጅቱ በእንግድነት እየቀረቡ ስለ ሃላፊነታቸውና ዓላማቸው ለማህበረሰቡ አባላት ንግግርና ውይይት እንዲያደርጉ መጠየቁም በትክክል አቶ ሳሙኤል ጌታቸው ምግብ ቤት ውስጥ በመጋበዝ በቃለ መጠይቅና በውይይት መልክ በጣም ትምህርታዊና ጠቃሚ የሆነ መልእክት እንዲንሸራሸር እያደረገ ነው::

ይህን ተመስጋኝ ጅምር የጠነሰሰው አቶ ሳሙኤል ጌታቸው የተባለ ወጣት ሲሆን የቅርብ ጓደኞቹ ገና ከጅምሩ ሃሳቡን እንደደገፉለትና ከጎኑ ቆመው እንዳበረታቱት ከሐዋርያ ጋር ባደረገው ቆይታ ገልጾልናል:: ጌታቸው ቀደም ብሎ ከሁለት ዓመት በፊት በኦታዋ ይኖር በነበረበት ጊዜ፥ "ለሀገራችን ኢትዮጵያ በበኩላችን ምን እንርዳ?" በሚል መሪ ሃሳብ ተነሳስቶ የኢርትዮጵያ ጓደኞች (Friends of Ethiopia) የሚል በጎ አድራጎት ድርጅት መሠረተ:: ከዚያም ከጓደኞቹ ጋር በመሆን አቅሙ በፈቀደ አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን በመግዛትና በማሰባሰብ ወደ ሀገር ቤት በመላክ በዚያው የሚኖሩ እርዳታ ፈላጊ ወገኖቻችንን ለመርዳት መሞከሩን አጫውቶናል::

"ኢትዮጵያን ፍራይደይ" የሚለው ሃሳብ የመጣለት ግን የዛሬው የአሜሪካ ፕረዚዳንት ባራክ ኦባማ (Barak Obama) ለአሜሪካው ፕረዚደንታዊ ውድድር እጩ ሆነው በሚወዳደሩበት ወቅት ከተመለከተው ተመክሮ ነው:: ሳሙአል በግሉ የባራክ ኦባማን እንዳለው ግለሰቦች በተሰለፉበት ጠንካራ እንዲሆኑ ከማለማመዱና ከማበራታቱ በላይ እግረ መንገዳቸውን የሚያስተላልፉት መልእክት በቀላሉ የሚገመት አይ ደለም::

# ኦንታሪዮ ትሪሊዩም ፋውንዴሽን (Ontario Trillium Foundation) የአፍሪካና ካሪቢያን ማህበረሰብ የብዙሃን መገናኛዎች ጋበዘ፤



ጥሪ የተደረገላቸው መገናኛ አባላት በከፊል ከፋውንዴሽኑ ባለሥልጣናት ጋር

ኦንታሪዮ ትሪሊዩም ፋውንዴሽን ከወትሮው ለየት ባለ ሁኔታ ለአፍሪካና ካሪቢያን ኮሚኒቲ የብዙሃን መገናኛ ተወካዮች የምሳ ግብዣና ያደረገ ሲሆን፥ በዕለቱ ስለ ፋውንዴሽኑ ዓላማና እንቅስቃሴ ሰፋ ያለ መግለጫ ተሰጥቷል::

የምሳ ግብዣውና መግለጫው የተሰጠው ቶሮንቶ ውስጥ 45 ቻርለስ ጎዳና (45 Charles St.) ላይ በሚገኘው ጽ/ቤቱ መሆኑ ሲታወቅ፥ ከአፍሪካና ከካሪቢያን ማህበረሰቦች (African & Caribbean communities) ጥሪ የተደረገላቸው የየማህበረሰቦቹ የብዙሃን መገናኛ ወኪሎች ተገኝተዋል:: የመግለጫው ዋና ሃሳብ እያደጉና እየሰፉ የመጡትን ሁለቱን ማህበረሰቦች (አፍሪካና ካሪቢያን) በተመለከተ ፋውንዴሽኑ አገልግሎቱን ለማስፋፋት ያለውን ፍላጎት ለመግለጽና በዚህ ጉዳይ ላይ ሃሳብ ለመለዋወጥ፥ የማህበረሰቦቹ ሰፊ አባላትም ይህን አገልግሎት የማስፋፋት እቅድ በብዙሃን መገናኛዎቻቸው አመካይነት እንዲተላለፍላቸው ለማሳሰብ ነበር::

በዛ ያሉ የሥራ ባልደረቦች በተገኙበት በዚህ የምሳ ግብዣ ውይይት፥ የኦንታሪዮ ትሪሊዩም ፋውንዴሽን ዋና ሥራ አስኪያጅ (CEO) የሆኑት ሮቢን ካርዶዞ (Robin Cardozo) ከሰጡት መግለጫና በውይይቱ ወቅት ከተነሱት ሰፊ ሃሳቦች መረዳት እንደተቻለው፥ ኦንታሪዮ ትሪሊዩም ፋውንዴሽን በአፍሪካና ካሪቢያን ኮሚኒቲዎች ውስጥ አዳዲስ ለትርፍ ሳይሆን ለተለያዩ ማህበረሰባዊ አገልግለት ተቋቁመው አገልግለት በመስጠት ላይ ያሉ ድርጅቶችን ለመደገፍ እንደሚፈልግ ግልጽ ሆኗል:: በነዚህ ማህበረሰቦች ውስጥ ያሉና ካሁን ቀደም ከፋውንዴሽኑ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ድርጅቶች የድጋፍ (fund) መጠየቂያ ማመልከቻዎቻቸውን ለጽ/በቱ በመላክ መመዘኛዎችን አሟልተውና ልቀው ከተገኙ ድጋፍ እንደማይለያቸው ተብራርቷል::

# በፍኖተ ዴሞክራሲ ሬዲዮ ሰኔ 27 ቀን 2001 ከተላለፈው የዜና ዘድገባ፤

- በደሴ ከተማ በወያኔ ፖሊሶች 7 ሰላማዊ ሰ -ችን በጥይት መገደላቸው እና 14 መቁሰላቸው ተዘገበ

- ከባህርዳር ህዝብ እንዲጨርስ በአያሌው ጎበዜ የቃል ትእዛዝ የመጣው ልዩ ሃይል
ሰላማዊ ሰው ላይ አልተኩስም በማለት ምላሽ ሰጠ

- የልዩ ሃይል አዛዥ እጁን በካቴና ታስሮ አዲስ አበባ ተወሰደ

- በሰራዊቱ ውስጥ የተጀመረው የምንጠራ ዘመቻ ተጠናክሮ ቀጥሎዋል

- በርካታ መኮንኖች ለቁም እስር እየተዳረጉ መሆኑ ተጋለጠ

- የፌዴራል ፖሊስ አድማ በታኝ በጦር ካምፕ ውስጥ ግምገማ አደረጉ ብዙ-ች ተባረሩ

ወደ ገጽ 22 ዞሯል

WORLDWIDE TRAVEL
በኛ በኩል ሲሄዱ ፀሐይ ለፀሐይ ነው መንገዱ!
Call us for all your travel needs.
Tel: 416-535-8872
851 BLoor St. West
TICO# 4642328

# ሐ ዋ ር ያ
# HAWARYA

ቅጽ 14 | ቁ. 3 | ፋክስ (905)799-2193 | ሰኔ/ሐምሌ 2001
Vol 14 | Issue 3 | Tel (416) 459-5964 | June/July 2009 | www.hawarya.net | hawarya.publications@sympatico.ca

### ህልም ህይወት፤

በሙቀቱ ቤቴ - መደብ ላይ ወለሉ፥
ቁንጫው ይምለጠኝ - አይማረኝ ትሁዋኑ፥
ሜዳ ላይ ከሚያሸኝ - ተባይ ምናምኑ
ከሚጫዎትብኝ ጊንጥና ጉንዳኑ።

ትልቁ ቤታችን - የተሠራው ድሮ፥
ጣራና ግድግዳው - የቆመው ተዋቅሮ፥
ወለል መደብ አለው - በደም'ብ ተዘጋጅቶ
ስንቱ የተኛበት - ክንዱን ተንተርሶ፤
ቢርበው ቢጠማው - ህልሙን ህይወት አርጎ።

-------
(ሙሉቀን)

# ካናዳ 142ኛ የልደት ቀኗን አከበረች!


በኦታዋ የተከናወነው ክብረ በዓል (The celebration in Ottawa)

በየዓመቱ 'የካናዳ ቀን' ተብሎ በሀገር አቀፍ ደረጃ በጁላይ ወር የመጀምሪው ዕለት (July 1) ተከብሮ የሚውለው የሀገሪቱ ብሄራዊ በዓል፥ በዚህ ዓመትም ረቡዕ ጁላይ 1/2009 (Wednesday, July 1, 2009) በከፍተኛ ድምቀት ተከብሮ ውሏል። በዚህ ዕለት ካናዳ እንደ አንድ ፌደራላዊ መንግሥት የተዋቀረችበትን 142ኛ ዓመት ያከበረች ሲሆን፥ ለአንድ አገር እድሜ በነዚህ በጣት በሚቆጠሩ ዓመታት ውስጥ፥ ሀገሪቱ ከፍተኛውን የእድገትና ሥልጣኔ እርምጃ ተራምዳለች።

ካናዳ በአንድ ፌደራላዊ ሥርዓት ሥር የዋለቺው ከጁላይ 1ቀን 1867 ዓ.ም (July1,1867) ጀምሮ ሲሆን፥ ይህም ህጋዊ አወቃቀር ከዚያ በፊት በሰሜን አሜሪካ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት የነበሩትን ኖቫስኮሻ (Nova Scotia), ኒውብራንስዊክ (New Brunswick) እና የካናዳ ክፍለ ሀገር ተብሎ ይታወቅ የነበረውና በሁዋላ በሂደት ኦንታሪዮና ኪዩቤክ (Ontario & Quebec) ተብለው የተሰየሙትን አራት ግዛቶች ያጠቃለለ ነበር።

የመጀምሪያው የአዲሷ ካናዳ ገቨርነር ጀኔራል የነበሩት ቻርለስ ስታንለይ ሞንክ፥ 4ኛው ቪስካውንት ሞንክ (Charles Stanley Monck, 4th Viscount Monck) ጁን 20 ቀን 1868 (June 20,1868) የፌደረሽኑ ቀን ካናዳዊያን በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲከብሩት የሚጠይቅ ዘውዳዊ አዋጅ ቢያስተላልፉም፥ ብሄራዊ በዓሉ በ1879 ዶሚኒዮን ቀን (Dominion Day) ተብሎ እስከጸናበት ጊዜ ድረስ መንግሥታዊ በዓል ሆኖ መከበር አልቻለም ነበር። በህግ ከጸደቀው የ'ዶሚኒዮም ቀን' በሁዋላም፥ ብሄራዊ በዓሉ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ጎልቶ ይከበር እንዳልነብር የታሪክ መዝገባት ያመለከታሉ። በጊዜው አብዛኛው የካናዳ ሕዝብ ሀገራዊና ወገናዊ ኩራቱን እንግሊዝአዊ አድርጎ ስለሚቆጥር፥ ለአዲሱ የካናዳ ሰውነቱ ብዙም ይጨነቅ እንዳልነበር ከተላለፉልን የታሪክ ቅርሶች መረዳት ይቻላል።

ካናዳ ዛሬ ልዩ ናት። እንደ ሕዝብ፥ ከዓለም አካባቢ በመጡ የተለያዩ የሰው ልጆች የተሞላች፥ በባህሏና የኢኮኖሚ አውታሮቿ የተቀየጠች ስትሆን፥ እንደ ሀገርም የራሷ ግዛትና መከላከያ ያላት የበለጸገች አገር ናት። ምንም እንኳ እሥካሁንም ዘውዳዊው የእንግሊዝ ሥርዓት የተቆራኛት ቢሆንም፥ በሀገሪቱ አስተዳደር ላይ ያለው ተፅእኖና ሚና ግን በጣም አነስተኛ ነው። እንደ ሌሎች ማህበረሰብ አባላት ሁሉ፥ እኛ መነሻችን ኢትዮጵያ የሆን ዜጎች ካናዳ ለዋለችልን ውለታ እናመሰግናለን፤ በአርቆ አሳቢ ልጆቿ የተገነባውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቷን ተጠቅመን ለተሟላ መብታችንና ጥቅማችን ስንታገል፥ በአኳያውም ደግሞ ክብሯንና ደህንነቷን ነቅተን እንጠብቃለን።

እንዲህም እየሆነ፥ ብሄራዊው 'የካናዳ ቀን' ከፍተኛ ወገናዊነትና ክብር እያገኘ በሀገሪቱ መዲናና በየክፍለ ሀገሮች ዋና ከተማዎች በድምቀት ተክብሮ እየዋለ ነው። በካናዳ ዋና ከተማ - ኦታዋ- በተከበረው የዘ ንድሮው ክብረ በዓል ላይ የሐዋርያ ዋና አዘጋጅ በቦታው ተገኝቶ በዕለቱ የተካሄደውን ከፍተኛ የአከባበር ሥነ-ሥርዓት ተከታትሏል።

ሐዋርያ ወደፊት ከዋናው ኢትዮጵያዊ ጉዳይዋ ጋር አያይዛ ካናዳ ውስጥ የሚካሄዱ ዋና ዋና ክስተቶችን ለአንባቢዎቿ ይዛ እንደምትቀርብ በዚህ አጋጣሚ እናስገነዝባለን። ካናዳ የሚቀጥለው ክረምት ወራት ኦሊምፒክ (winter Olympic) አስተናጋጅ እንደመሆኗ መጠን፥ በቦታው ተገኝተን ለመዘገብ ዕቅድ አለን።

---

### ሙዚቃ አፍቃሪዎች ተረጋጉ፤

## ማይክል ጃክሰን እንደ ጥላሁን ገሰሰ ህያው ነው!!


የማይክል ጃክሰን የመጨረሻው ገጽታ
(The last face of Michael Jackson)

የሰው ልጅ በመጠቀ ጥበቡ ገና ፈትኖ ያላረጋገጠው ነገር ቢኖር ስንት ዓይነት ሞት መኖሩን ነው። ጀግኖች ከሚሊዮኖች ተመርጠው ለሀገርና ሕዝብ ደጀን ሆነው በፍልሚያው ቦታ ግምባራቸውን እማኝ ሰጠው ሲወድቁ፥ ሞቱ ይባላሉ፤ እንዲሁም፥ የማይታሰበውን አልመው፥ የማይቻለውን ችለውና አረጋግጠው የታወቁና ለሰው ልጆች የደስታ ስሜት ተጨናቂ የሆኑ ድንገት ከመድረኩ ዞር ሲሉ፥ 'ሞቱ' የሚል ነጋሪት ይጎሰማል። በዚሁ ልክ ደግሞ፥ ኑሮውን የመረጠ ዛርጤ፥ ለእውነትና ለሃቅ ደንገጡር ለመሆንና ደፍሮ ለመቆም ሃሞት ያልፈጠረበት የዚህች ዓለም አምላኪ፥ ወይም ስንፍናና አልባሌ ልምድ ተብትበው በመያዝ ህይወቱን ጥገኛና ተሸናፊ ያደረጉት ገምቱ ስትንፋሱ ስትቋረጥ ልክ እንደሌሎች 'ሞተ' ይባላል። መሞት ማለት የዚህን ዓለም ሽታና ጨገሬታ አጥቶ በአካል መሰወር ከሆነ፥ የሞተው ማነው? ከተሰወሩ በሁዋላ እልፍ አእላፍ ሥራዎቻቸውና ምግባራቸው የሚወደሱላቸው፥ ወይስ የህይወት ዘመናቸውን ባግባቡ ባለመጠቀማቸው ቀሪ ምልክት ሳይተክሉና የሰውን ልጅ ባህሪ ሃሳብ ሳያንኳሉ እልም ድርግም ያሉት?

ለዚህ ነው ማይክል ጃክሰን እንደ ትናንቱ ብርቅ የኢትዮጵያ ልጅ ጥላሁን ገሰሰ አልሞተም ማለት የሚያስደፍረው። ዓለም የህይወት ትግል አውድማ መሆኗን የተረዱት የማይክል ወላጆች ገና በጥዋት የልጅነት ዕድሜው፥ ባዘጋጁለት መድረክ ላይ ጨዋታውን አጠናቆ ዘላለማዊ ህይወትን ተጎናጽፏል። አንጨብጠውና አንዳስሰው ይሆናል እንጅ፥ ማይክል ጃክሰን በብዙዎቻችን ዘንድ ከእይታችንም ሆነ ከህሊናችን የሚሰወር ከቶ አይደለም።

ማይክል ጃክሰን ምንም እንኳ ዘግየት ብሎ የሙዚቃ አፍቃሪዎቹን ልብ ያልነካ የተለያዩ የባህርይ ለውጦች የታዩበት ቢሆንም፥ የሙያው ሙሉ ባለቤትና እፍቃሪ ሆኖ በአይታክቴነት ያበረከታቸው ድንቅ የሙዚቃ ሥራዎቹ ግን

ወደ ገጽ 23 ዞሯል

## የኢትዮጵያዊያን ማህበር በቶሮንቶ ዓመታዊ ስብሰባውን አካሄደ


በስብሰባው ላይ የተገኙ የማህበሩ አባላት

በካናዳ ደረጃ በታላቅነቱና በተግባራዊ እንቅስቃሴው በጉልህ የሚታወቀው የኢትዮጵያዊያን ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው ባለፈው ሜይ 31 ቀን 2009 ዓመታዊ ስብሰባውን አካሂዷል። በዕለቱ ከአብዛኛው ተመሳሳይ ዓመታዊ ጉባኤዎቹ ሻል ባለ ሁኔታ በዛ ያሉ የቆዩና አዳዲስ አባላቱ የተሳተፉ ሲሆን፥ በቁጥር ደረጃ ሲታይ እሰየው የሚያሰኝ ነበር።

በጉባኤው መግቢያ ላይ የማህበሩ ፕረዚዳንት ዶ/ር ቡሻ ታኣ የማህበሩን ህገ-ደንብ ተመርኩዘው ቦርዱ ያከናዎናቸውን የሥራ እንቅስቃሴዎችና ወደፊት ያቀዳቸውን ተግባራት ዝርዝር ማብራሪያ የሰጡ። የማህበሩ ዋና ሥራ እስኪያጅ የሆኑት ዶ/ር

ወደ ገጽ 22 ዞሯል